# የESIT እይታ እና የመስማት ችሎታ ማጣርያ፦

## የባለ ሦስት አቅጣጫዊ አቀራረብ የቤተሰብ መመሪያ



***ማንኛውም ሕጻን አይኑን እና የጆሮውን የመስማት ችሎታ ለማስመርመር ገና ሕጻን ነው የሚባል አይደለም።***

### እያታን እና መስማትን ለምን ማጣራት አስፈለገ?

**እይታ እና የመስማት ችሎታ ልጆች ስለ ዓለማቸዉ የሚማሩበት ወሳኝ መንገዶች ናቸው። የመስማት እና የእይታ ስጋቶችን አስቀድሞ ማግኘቱ ልጅዎ እንዲበለጽግ ያግዘዋል። የሚፈልጉትን አይነት እርዳታ፣ ከመጀመርያው ማግኘት ይችላሉ።**

### የባለ ሶስት አቅጣጫዊ አቀራረብ ምንድነው?

**የባለ ሦስት አቅጣጫዊ አቀራረብ ለEarly Support for Infants and Toddlers (ለጨቅላ ሕጻናትዎ እና ታዳጊዎችዎ የሚሰጥ የቅድመ ድጋፍ፣ ESIT) አገልግሎት አቅራቢ ስለልጅዎ እይታ እና የመስማት ችግር እንዴት እንደሚፈትሽ ነው። ይህም መደበኛ የሆነ ፈተና አይደለም እንዲሁም ከጆሮ ወይም ከዓይን ሐኪም የተሟላ ግምገማ ቦታ መውሰድ የለበትም። ባለ ሶስት አቅጣጫዊ አቀራረብ፣ ልጅዎ ሙሉ የማየት ወይም የመስማት ግምገማ እንደሚያስፈልገው ማወቅ እንችላለን።**

### በባለ ሶስት አቅጣጫዊ አቀራረብ ወቅት ምንድን ነው የሚፈጠረው?

የESIT አቅራቢዎ የሚከተሉትን ያደርጋል፦

- ልጅዎ እንዴት እንደሚያይ እና እንደሚሰማው ስለሚያሳስብዎት ነገር ከእርስዎ ጋር ይነጋገራል።
- ልጅዎ ሲጫወቱ እና የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ የማየት እና የመስማት ችሎታቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙ ይመለከታል።
- የልጅዎን የሜዲካል መዝገቦች ይመልከቱ። ዶክተርዎ ስለ ልጅዎ ጤና እና እድገት ምን እንደነገረዎት ይጠይቁዎታል።

### ከሶስት አቅጣጫዊ አቀራረብ በኋላ ምንድን ነው የሚፈጠረው?

ልጅዎ እንዴት እንደሚያይ ወይም እንደሚሰማው፣ እርስዎ እና የእርስዎ የESIT አገልግሎት አቅራቢ እንዴት የመከታተያ እቅድ እንደሚያደርጉ የሚያሳስቡ ማንኛቸውም ነገሮች ካሉ። ይህ እቅድ በህክምና(ሜዲካል) አገልግሎት ሰጪዎች እና/ ወይም በESIT አቅራቢ ልዩ ትምህርትን ሊያካትት ይችላል።

### ምን ያህል ያስከፍላል?

እርስዎ ምንም የሚከፍሉት ክፍያ የለም። ይህ Three-Pronged Approach (ባለ ሶስት አቅጣጫዊ አቀራረብ) የነጻ ESIT ግምገማ ሂደት አካል ነው።

### ተጨማሪ ጥያቄዎች አሉት?

በልጅዎ እድገት ላይ እርስዎን ለመደገፍ ቁርጠኞች ነን። ምንም አይነት ጥያቄ ካልዎት፣ እባክዎን የESIT አቅራቢዎን ይጠይቁ።

---

*DCYF አድሎ አይፈጽምም እንዲሁም ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ እምነት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ዕድሜ፣ የአርበኛነት ሁኔታ ወይም ማንኛውም የአካል፣ የስሜት ህዋሳት ወይም የአዕምሮ እክል ሳይኖር ለሁሉም ሰው ፕሮግራሞቹን እና አገልግሎቶቹን በእኩልነት ያቀርባል።*

*የዚህን እትም ነጻ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎን የDCYF Constituent Relations ( የDCYF የመሰብሰቢያ ግንኙነቶችን) በ 1-800-723-4831 ወይም በኢሜል* ***communications@dcyf.wa.gov***.

DCYF PUBLICATION EL_0069 AM (05-2023) Amharic

Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES